**የደቡብ ኪንግ ካውንቲ የገንዘብ ድጋፍ ፣ ክልላዊ ማገገም ላይ ለሚያተኩሩ ፕሮጀክቶች የመጀመሪያውን የእርዳታ ዑደት ጀመረ።**

**በፍጥነት ለመልቀቅ | ኦገስት 3, 2020**

**Contact**: Perry Cooper | SEA Airport
(206) 787-4923 | cooper.p@portseattle.org

**ሲያትል** - Port of Seattle በፍትሃዊነት ላይ የተመሠረተ ሽርክናን ለማዳበር እና ሀብቶችን እና ድጋፍን በአውሮፕላን ማረፊያው አቅራቢያ ላሉ ማኅበረሰቦች ለማቅረብ የተቋቋመውን የደቡብ ኪንግ ካውንቲ የገንዘብ ድጋፍ የመጀመሪያ ዑደት ዛሬ ጀመረ። ወደቡ ከዛሬ እስከ 2023 ባለው ጊዜ ውስጥ 10 ሚሊዮን ዶላር ቃል ገብቷል ፤ ለ2020 ከዛሬ ጀምሮ 1 ሚሊዮን ዶላር ይገኛል። የገንዘብ ድጋፉ የመጀመሪያ የእርዳታ ዑደት ከ COVID-19 ወረርሽኝ ተፅእኖዎች የክልሉን መልሶ ማገገምን መደገፍ ላይ ያተኩራል ።

"የዓለም ጤና እና ምጣኔ ሀብት ቀውስ በጣም ተጋላጭ የሆኑ ማኅበረሰቦቻችንን እጅግ በጠነከረ መልኩ ለመምታት እንደቻለ" Port of Seattle Commission President Peter Steinbrueck ተናገረ። በምጣኔ ሀብታችን እና በአካባቢያችን ውስጥ ኢ-ፍትሃዊነትን ለማስተካከል የደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍን መስርተናል። የክልሉ ምጣኔ ሀብት እየተባባሰ የመጣ የምጣኔ ሀብትና የጤና ቀውስ ገጥሞታል--የደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍም ኢ-ፍትሀዊነትን ለመድረስ እና እጅግ አስፈላጊ በሆነበት ቦታ አዲስ የምጣኔ ሀብት ዕድሎችን ለመፍጠር የታሰበ ነው።

የገንዘብ ድጋፎቹ የሚደግፉት አሁን ባለው የምጣኔ ሀብት ቀውስ በጣም የተጎዱ ማኅበረሰቦችን ፤ ከወደብ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ኢንዱስትሪዎች ጋር በተገናኙ ፕሮጀክቶች ፤ የአየር በረራ ሥራን ፣ የባህርን ፣ የግንባታ ንግዶች እና የአካባቢያዊ ሥራ እንዱስትሪዎችን ጨምሮ ይሆናል።

"የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለነባር መዋቅራዊ ውድቀቶች እና ማኅበራዊ ኢ-ፍትሀዊነቶችን በማጋለጥ ፣ ሥር እንዲሰድ እና እንዲባባስ በማድረግ ባለቀለም ማኅበረሰቦች ላይ ፣ ሴቶች ላይ ፣ ስደተኞች እና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል" ብለዋል የእኩልነት ፣ ልዩነት እና አካታችነት ጽ / ቤት ዋና ዳይሬክተር Bookda Gheisar "የደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍ በማኅበረሰባችን ውስጥ ያለውን ወሳኝ ፍላጎት የሚያሟላ እና በብዛት ተጽዕኖዎች ባጋጠሟቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ከአንዳንድ አስፈላጊ የምጣኔ ሀብት እና ከሰው ኃይል ጋር የተገናኙ ጥረቶችን መደገፍ ላይ ያነጣጠረ ነው።"

Port of Seattle የደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍን በ2019 የመሠረተው በፍትሃዊነት ላይ የተመሠረተ ሽርክናን ለመደገፍ እና ሀብት እና ድጋፍን ለእነዚህ ማኅበረሰቦች ለመስጠት ነው። የገንዘብ ድጋፉ አየር ማረፊያ አካባቢ ባሉ ማህበረሰቦች የጩኸት ሁኔታን ለማቃለል ፣ ለአካባቢ ጤና እና ዘላቂነት መልስ በመስጠት ይደርሳል።

ለኮቪድ-19 ቀውስ አስከፊ ተፀዕኖ ምላሽ ለመስጠት እንዲሆን የ Port Commission ለደቡብ ኪንግ ካውንቲ ገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ ትኩረት የምጣኔ ሀብት ልማትን አክሏል። ከሁሉም የዋሽንግተን ቁልፍ የምጣኔ ሀብት ዘርፎች ጋር ባለው ትስስር እና በእኛ ተቋማት ውስጥ ከሚሰሩ ከ 500 በላይ አሠሪዎች ጋር በተገናኘ ፣ የክልሉን መልሶ ማቋቋም ለመምራት እንዲረዳ ወደቡ በተለየ ሁኔታ የቆመ ነው።

የገንዘብ ድጋፉ ዉጤታቸዉ ከወደብ የተገናኙ እንዱስትሪዎች ዉስጥ የሰው ኃይል ልማት ፣ ስራ ፈጠራ ፕሮግራሞች ወይንም የኢኮኖሚ ማገገሚያ መፍትሔዎች ጋር የተገናኙ ፕሮጀክቶች አመልካቾችን ይጋብዛል። ፕሮቸክቶቹ በአየር ማረፊያ አቅራቢያ ያሉ ማኅበረሰቦችን ፤ ለምሳሌ፡ ቢዩሪየን ፣ ዴ ሞይን ፣ ፌደራል ዌይ ፣ ኖርመንዲ ፓርክ ፣ ሲ-ታክ እና ተኩዊላ ከተሞች መጥቀም ይኖርባቸዋል። ፕሮጀክቶቹ በምጣኔ ሀብት ሁኔታ ተጋላጭ የሆኑትን እና ታላላቅ ፈታኝ ሁኔታ ያጋጠሟቸውን ሰዎች ፣ እንዲሁም ባለቀለም ሰዎችን ፣ የአገሬው ሰዎችን ፣ ስደተኞችን እና መጤዎችን ፣ ዝቅተኛ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያላቸውን ፣ ዘማቾችን ፣ አዛውንቶችን ፣ ወጣቶችን ፣ እና/ወይም አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ማገልገል አለባቸው። በእነዚህ የመርሐ ግብር ዘርፎች ውስጥ የሚሠሩ የማኅበረሰብ ድርጅቶች ፣ የንግድ ክፍሎች እና ሌሎች ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ለማመልከት ብቁ ናቸው።

1 ሚሊዮን ዶላር የድጋፍ ገንዘብ ያለ ሲሆን የእርዳታ ጥያቄዎች እስከ $100,000 ድረስ ሊሆኑ ይችላሉ ።ማመልከቻዎችን እስከ መስከረም 30 2020 እኩለ ቀን 12 ሰዓት ድረስ ማስገባት ያስፈልጋል።

ተጨማሪ ዝርዝሮች እና የማመልከቻ ሰነዶች www.portseattle.org/programs/south-king-county-fund ላይ ይገኛሉ ።

**ስለ Port of Seattle**

በ1911 በህዝብ ምርጫ እንደ ልዩ ዓላማ መንግሥት የተመሠረተው የPort of Seattle ተልእኮ ፤ ንግድን ፣ ጉዞን ፣ የንግድ ሂደትን እና ፍትሃዊ ፣ ተጠያቂነት እና አካባቢያዊ ኃላፊነት ባለው መንገድ ሥራ ፈጠራን በማስፋፋት የምጣኔ ሀብት ዕድል እና የሕይወት ጥራትን በክልሉ ለማስተዋወቅ ነው።

ወደቡ የ Seattle-Tacoma International Airport እንዲሁም የ North Pacific የዓሳ ማጥመጃ ስብስቦችን እና የህዝብ ማሪና መኖሪያ የሆነውን የ Fishermen's Terminal ባለቤትነት ያለው እና የሚያሠራ ነው። ወደቡ ከ Northwest Seaport Alliance ጋር ባለው አጋርነት ሁለት የመርከብ ማረፊያ ጣቢያዎች ፣ የእህል ማረፊያ ጣቢያ ፣ የሪል ስቴት ንብረቶች እና የባህር ጭነት ማረፊያ ጣቢያዎች አሉት።

የወደብ ክንውኖች በክልሉ ውስጥ ወደ 200,000 የሚጠጉ የሥራ መደቦችን እና 7 ቢሊዮን ዶላር የደመወዝ ክፍያን ለመደገፍ ይረዳሉ። በሚቀጥሉት 17 ዓመታት ውስጥ ፣ የወደቡ "Century Agenda" በምጣኔ ሀብት እድገት አማካይነት እና የሀገሪቱ መሪ አረንጓዴ እና ኃይል-ቆጣቢ ወደብ በመሆንም ጭምር ተጨማሪ 100,000 ሥራዎችን ለመፍጠር ይፈልጋል። ተጨማሪ ለማወቅ *www.portseattle.org*

# # #